# ራስ ገዝ ቤተክርስቲያን

## የቤተክርስቲያን ተከላ ጥናት

ከኢንተርናሽናል ኮርስፖንዳንስ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በላሪ ፔት ተዘጋጅቶ በሥነ መለኮት በቤቴ አማካኝነት ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የተመለሰ በቤተክርስቲያን ተከላ ላይ መትከል የተዘጋጀ የመማሪያ መጽሐፍ።

**Starting New Churches**

ሁለተኛ ዕትም

ያሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው ።

1999 - አዲስ አበባ

## ማውጫ

ገጽ

መግቢያ ........ 1

**ክፍል አንድ የቤተ ክርስቲያን ተከላ ምሳሌ**

1. የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ........ 3
2. ቤተክርስቲያንና ተልዕኮዋ ........ 28

**ክፍል ሁለት የቤተ ክርስቲያን ተከላ ስልት**

3. ራስን በራስ ማስተዳደር ........ 49
4. ራስን በራስ ማስፋፋት ........ 71
5. ራስን በራስ መደገፍ ........ 89

**ክፍል ሶስት ቤተ ክርስቲያንን ማባዛት**

6. መሪዎችን ማሠልጠን ........ 107
7. የቤተክርስቲያን ተከላ ዘዴዎችና ምሳሌዎች ........ 125
8. ቤተክርስቲያንን የማባዛት ዕቅድ ........ 140

ለ. አዳዲስ ክርስቲያኖች ወደ ቤተክርስቲያን መጥተው ስለ ክርስቲያናዊ አኗኗር ይማራሉ፣ ከዚያም እነርሱ ራሳቸው ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ያመጣሉ።

ሐ. የቤተክርስቲያን ዋናው የሥራ ድርሻ በየመንገዱና በየአደባባዩ ወንጌልን ማስፋፋት ነው።

መ. ቤተክርስቲያን የወንጌል ማስፋፋት ድርሻዋን የምትወጣው ሌሎችን በማስተማርና ደቀመዛሙርት በማድረግ የሚያቋርጥ እንቅስቃሴ ነው።




# የቤተክርስቲያን አገልግሎት

## ሁለቱ የአገልግሎት ተግባሮች

### *ዓላማ 4 የቤተክርስቲያን አገልግሎት ዓላማ ምን እንደሆነና እንዴት አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን መትከል እንደሚቻል መግለጽ*

እስካሁን ሁለት የቤተክርስቲያን ተግባራትን ተመልክተናል። እነዚህም ተግባራት 1) ወንጌል ማስፋፋትና 2) ማስተማር ናቸው፤ ሌሎች ምክንያቶች ቢኖሩም የቤተክርስቲያን ሕልውና በዋናነት ያስፈለገው እነዚህን ሁለት እንቅስቃሴዎች ተግባራዊ ለማድረግ ነው። እነዚህ ሁለት እንቅስቃሴዎች ቤተክርስቲያን ለዓለም ከምትሰጠው አገልግሎት ዋነኞቹ ናቸው።



## የአገልግሎት ስጦታ ዓይነቶች

ኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎቱን ሲጨርስ መንፈስ ቅዱስ መጣ፤ ለቤተክርስቲያንም የአገልግሎት ስጦታዎችን ሰጠ፤ ቤተክርስቲያን ከእግዚ አብሔር የተሰጣትን ጥሪ የምትወጣውም በእነዚህ የአገልግሎት ስጦታዎች በመታገዝ ነው። ይህ ግን እንዴት ነው የሚሆነው? በቤተክርስቲያን ውስጥ ማን በየትኛው አገልግሎት ማገልገል እንዳለበት የሚወስነው ማነው? ለቤተክርስቲያን ስለተሰጡት የአገልግሎት ስጦታዎች ባሕርይና ዓላማ የሚያመለክቱትን ጥቅሶች አንብባቸው። ሮሜ 12:5-8፤ 1ቆሮ 12:27-31፤ 1ጢሞ 3:1-10 እና ኤፌ 4:11-12።

ጥቅሶቹ እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ካደላት የአገልግሎት ስጦታ ዓይነቶች ምሳሌ የሚሆኑትን አካትተዋል። እነዚህን ስጦታዎች ጥቅም ላይ ከሚውሉበት ሥፍራ በመነሳት ልንመድባቸው እንችላለን።

1. በቤተክርስቲያን ውስጥ በዋነኛነት የምንጠቀምባቸው የአገልግሎት ስጦታዎች፡ ነቢያት፣ መጋቢዎች፣ አስተማሪዎች፣ ሽማግሌዎች፣ ዲያቆናት፣ አስተዳዳሪዎችና ልዩ ልዩ ልሳናት
2. ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ለአገልግሎት የሚውሉ ስጦታዎች ሐዋርያትና ወንጌል ሰባኪዎች
3. በቤተክርስቲያን ውስጥና ከቤተክርስቲያን ውጪ የምንጠቀምባቸው የአገልግሎት ስጦታዎች፡ ማጽናት፤ ተአምራትን ማድረግ፤ መስጠት የፈውስ ስጦታዎች፤ ምሕረት ማድረግና እርዳታ ናቸው።

ምንም እንኳ የአገልግሎት ስጦታዎችን ከላይ በተመለከትነው መልክ ብንመድባቸውም እንደ አስፈላጊነቱ ሁሉም በቤተክርስቲያን ውስጥ ሊሰሩ ይችላሉ፤ እንዲሁም ደግሞ እንደ አስፈላጊነቱም ከቤተ ክርስቲያን ውጪ አገልግሎት ላይ መዋል ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል ወንጌላዊው ክርስቲያኖችን ወንጌል ስለማስፋፋት በቤተክርስቲያን ውስጥ ማስተማር ይችላል። መጋቢውም ለክርስቲያኖች እንደሚያደርገው ሁሉ ከቤተክርስቲያን ውጪ ላሉ ሰዎች መስበክና ማስተማር ይችላል። ከላይ በተመለከትነው ምድብ የአገልግሎት ስጦታዎችን የመደብንበት ምክንያት እያንዳንዱ አማኝ የሚሰራው ሥራ እንዳለውና ለዚህ የሚያስፈልገውም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠው መሆኑን ለማሳየት ነው።

(6). የሚከተሉትን ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ አንብብና ከእያንዳንዱ ጥቅስ ያገኘኸውን የስጦታ ዓይነት ጻፍ፦

ሀ. ሮሜ 12:6 ________________
ለ. ሮሜ 12:7 ________________
ሐ. 1ቆሮ 12:8-10 ________________
መ. ኤፌ 4:11 ________________

## የመከራ ፈተና

ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሚሆነውን ፊደል ክበበው።

1. የቤተክርስቲያንን ተልዕኮ እንዲህ በማለት መግለጽ ይቻላል።

ሀ. የወንጌል መልእክተኞችን በየሀገሩ ሁሉ መላክ።
ለ. የእግዚአብሔርን የደህንነት ዓላማ ለሰዎች ሁሉ መንገር።
ሐ. በአካባቢዬ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን መመሥረት።
መ. በሁሉም አገር ላሉ የቤተክርስቲያን መሪዎች ስልጠና መስጠት።

2. ሐዋርያት በጊዜያቸው በፍጥነት ቤተክርስቲያን መመሥረት የቻሉበት ምክንያት

ሀ. አይሁዳውያን ኢየሱስ መሲህ መሆኑን ለመቀበል ዝግጁ ስለነበሩ ነው።
ለ. በምኩራብ ውስጥ ተደማጭነት ያላቸው መሪዎች ስለነበሩ ነው።
ሐ. የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ስለተቀበሉ ነው።
መ. በመንግሥት ባለሥልጣኖች የሚከበሩ ሰዎች ስለነበሩ ነው።

3. የጥንት ቤተክርስቲያን ማደግ የቻለችው ሐዋርያቱ ምን ያደርጉ ስለ ነበር ነው?

ሀ. የሙሴን ሕግ በመጥቀሳቸውና ኢየሱስ ሕጉን መጠበቁን በማረጋገጣቸው ነው።
ለ. የኢየሱስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሳኤ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ፍጻሜ መሆኑን በማስተማራቸው ነው።
ሐ. ኢየሱስን ባለመቀበላቸው አይሁዳውያንን ስላወገዙና በንስሐ እንዲመለሱ ጥሪ ስላቀረቡላቸው ነው።
መ. ለሁሉም ባሕሎች የሚስማማ አምልኮን በመስበካቸው ነው።

4. የቤተክርስቲያን መሪዎች ምን ያህል በእግዚአብሔር ይደገፉ እንደ ነበር ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያቀርቡት ማረጋገጫ

ሀ. በቤተ መቅደሱ በር ላይ እንደተፈወሰው አንካሳ የፈውስ ተአምር በመፈጸሙ፣
ለ. በሰማሪያ ፊሊጶስ አጋንንትን ከብዙ ሰዎች በማስወጣቱ፣
ሐ. ሐዋርያቱ የተለያዩ አገሮች ቋንቋዎችን መናገርና መረዳት መቻላቸው፣
መ. "ሀ" እና "ሐ"　　　　　ሠ. "ሀ" እና "ለ"

5. የተለያዩ ባሕል ያላቸው ሰዎች ወንጌልን የተቀበሉበት ምክንያት፡-

ሀ. ሐዋርያቱ የማንንም ባሕል ሳይንቁ ደህንነት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ መሆኑን በመናገራቸው ነው።



ለ. ቤተክርስቲያን የማንኛውንም ሃይማኖት አምልኮ ክርስቲያናዊ ትርጉም በመስጠት ለመቀበል ዝግጁ ስለነበረች ነው።
ሐ. ክርስቶስን መቀበል ምንም ዓይነት የእምነት መግለጫ ማውጣት ስላላስፈለገው ነው።
መ. ክርስትና ምንም ዓይነት መከራ የሌለበት በመሆኑ ነው።

6. ከሚከተሉት ውስጥ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ያልተከተለችው የትኛውን ነው?

ሀ. ድርጅታዊ መዋቅሩ የተዘረጋው በቤተክርስቲያኑ ችግር መሠረት ነበር።
ለ. መስጠት የአምልኮ አንዱ ክፍል በመሆኑ ቤተክርቲያን በአማኞች ገንዘብ ስጦታ ትደገፍ ነበር።
ሐ. የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ እቅድ የሚወጣውና ሥራ ላይ የሚውለው በሐዋርያው ጴጥሮስ ነበር።
መ. በመጀመሪያ ቤተክርስቲያኖች በዋና ከተሞች ይመሰረቱ ነበር።

7. የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 6 ላይ ያለው ገለጻ በረዳት መሪነት ያገለገሉት የመጀመሪያዎቹ አገልጋዮች ለሥራው ብቁ የሆኑና

ሀ. ከሚመሩዋቸው ሰዎች ጋር አንድ ዓይነት ኤኮኖሚያዊ ደረጃ እንደ ነበራቸው ያሳያል።
ለ. መናናቅ እንዳይፈጠር ከቡድኑ ውጪ ባሉ ሰዎች መመረጣቸውን ያሳያል።
ሐ. በሚመሩዋቸው ሰዎች ተቀባይነት እንደነበራቸው ያሳያል።
መ. ያለ ምንም የበላይ ባለሥልጣን መሥራት እንደሚችሉ ያሳያል።

8. በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 የተገለጸው የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ሸንጎ የሚከተሉትን የአስተዳደር ምሳሌዎችን ያካተተ ነበር። ባለሥል ጣኖቹ የሸንጎው መሪዎች ነበሩ፣ የሥልጣን ክፍፍል ነበር፣ ለሸንጎው ሪፖርት ይደርሰው ነበር፣ በችግሮቹና በሚወጡ መመሪያዎች ላይ ይወያዩ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ

ሀ. ሸንጎው በየሁለት ዓመቱ ለመሰብሰብ ውሳኔ ይደርግ ነበር።
ለ. ውክልና ያላቸው ሰዎች ለቤተክርስቲያን ሪፖርት ያቀርባሉ፣ ወይም ውሳኔውን አስመልክቶ በጽሑፍ የሰፈረ ሪፖርት ይደርሳቸዋል።
ሐ. ባለሥልጣኖችን የሚመርጡበት ዘዴ ነበራቸው።
መ. ለመጋቢዎች የክብነት ሹመት ይሰጣቸዋል።

9. አንዳንድ ተግባሮችን በተመለከተ ክርስቲያናዊ መለኪያዎችን ሊያስተምራቸው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ጽፎላቸዋል። ከሚከተሉት አንዱ ግን የጳውሎስ ትምህርት አይደለም፣ የጳውሎስ ትምህርት ያልሆነው የትኛው ነው?

# ራስን የማስተዳደር እንቅስቃሴ

## መመዘኛዎችን መቀበል

### *ዓላማ 2 የራሳቸውን አጥቢያ ቤተክርስቲያን እንዲያስተዳድሩ አዳዲሶች አማኞችን ማዘጋጀት*

ቤተክርስቲያን የተከለው ሰው አዳዲስ አማኞችን በማሰባሰብ፤ ለለ ክርስትና እምነት ያስተምራቸዋል። ከትምህርቱ ዓላማዎች አንዱ ራሳቸውን የአጥቢያ ቤተክርስቲያን እንዲያደርጉ መርዳት ነው። አዲሶቹ አማኞች በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ደረጃ እንዲደራጁ የቤተክርስቲያኒቱ ተካይ ሊከተላቸው የሚገቡ እርምጃዎች ምንድን ናቸው?

በመጀመሪያ የክርስትና እምነት የተመሰረተው በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ መሆኑን አማኞቹ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል። በ1ኛ ጴጥ 3:15 የተሰጠው ትምህርት አማኞች እምነታቸውን በእግዚአብሔር ቃል ላይ መመሥረታቸው አስፈላጊ እንደሆነ ያመለክታል፤ "… ክርስቶስን በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ" ይላል። አማኞች መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን ሲረዱና በየዕለቱ በሕይወታቸውም ተግባራዊ ሲያደርጉ የቤተ ክርስቲያንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በአንድነት ይሰራሉ።

ከዚህም በተጨማሪ የአማኞች ባህሪና እምነት መለኪያዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆን አለባቸው። መሠረታዊ የእምነት መግለጫዎችን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማወቅ ወይም አዳዲስ ሕጎችን መማሩ በቂ አይደለም። አዳዲሶቹ አማኞች መጽሐፍ ቅዱስ እንድንኖረው የሚፈልገውን ኑሮ እንዲረዱና በሕይወታቸውም ተግባራዊ እንዲያደርጓቸው በትዕግሥት ማስተማር ይገባል። እንደ ሁኔታው አስፈላጊነት እነዚህን ትምህርቶች የሕይወታቸው ክፍል አድርገው እስኪቀበሏቸው ድረስ ትምህርቱ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። በመተከል ላይ ያለቸው የራሳቸው ቤተክርስቲያን ከሆነች፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ የራሳቸው መለኪያ ሚዛንም ሊኖር ይገባል።
አማኞቹ የክርስትና እምነታቸውን በሚገባ መግለጽ ከቻሉ ለክርስቲያናዊ ሕብረታቸውም መሠረት ይኖራቸዋል። እንዲት እውነተኛ ቤተ ክርስቲያንን ለመመሥረት ከተፈለገ ሁሉም አማኞች የሚቀበሏቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑና የሥነ-ምግባር መለኪያዎች ሊኖሩ ይገባል።

ዛሬ በየትኛውም አገር ቢሆን ሐሰተኛ መምህራን አሉ፤ የሕብረታችን መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ልንል እንችላለን። ብዙዎቹ የሐሰት ሃይማኖቶች የሚሉትም ይህንኑ ነው። እንደ ክርስቶስ አካልነት በስምምነት መሥራት ከተፈለገ ለሕብረታችን መለኪያ ሚዛን ሊኖረው ይገባል (1ቆሮ 1:10)። ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው የቤተክርስቲያን አባል ከመሆኑ በፊት



ዳግም መወለድ አለበት የሚለው በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው መስፈርት ነው። በክርስቶስ ባገኘው አዲስ ሕይወትም መሠረት ሕይወቱን መምራት አለበት። እንደ አካባቢው ባሕል መሠረት አማኞች አንዳንድ ስምምነት ላይ መድረስ ይችላሉ፤ ለዚህ መመሪያ የሚሆናቸው ግን መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ነው።

ቤተ ክርስቲያን የሚተክል ሰው አማኞችን በቤተክርስቲያን ደረጃ ሊያሰባስብ አንዳንድ ባሕላዊ ችግሮች ሊገጥሙት ይችላሉ። ከእነዚህ ብዙዎቹ በጣም አደገኛና ሥር የሰደዱ ችግሮች ሊሆኑ ይችላሉ፤ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያ መሠረት መፍትሔ ለመሻት ብዙ ውይይት ማድረግና በትዕግሥት ማስተማርን ሊጠይቁ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል በአንዳንድ አገሮች ከክርስቲያናዊ ትምህርት ጋር የማይስማሙ የጋብቻ ባሕሎች አሉ። በአንዳንድ አገሮች ደግሞ የመንግሥትን ግብር ማጭበርበር፣ መሥረቅና ጉቦኝነት በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አላቸው። በአንዳንድ አገሮች ክርስትና በሕግ ወይም በማሕበረሰቡ የማይፈቀድ ሃይማኖት ነው። ለእንደዚህ ዓይነት ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት ብዙ ጸሎትንና የመንፈስ ቅዱስንም ምሪት በትጋት መጠየቅ ያሻዋል። እነዚህ አስቸጋሪ ባሕሎችን በተመለከተ መንፈስ ቅዱስ ለአማኞቹ ምሪት ሲሰጣቸው፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተመሠረተ መለኪያ ሚዛን ይኖራቸዋል።

(3). ካለፈው ውይይታችን አዳዲስ አማኞች ራስ ገዝ ቤተ ክርስቲያንን ለመትከል ሊደረግላቸው ሲ፤ሚባ እገዛ ተምረናል። ይህን ማድረግ የሚችሉትም

ሀ. የክርስትና ሕይወት በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ሲረዱ ነው።
ለ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያዎችን የግላቸው ሥነ-ምግባርና እምነት መለኪያ አድርገው ሲቀበሉ ነው።
ሐ. መሠረታዊ አስተምሕሮዎች የሕብረታቸው መሠረት መሆናቸውን ቢስማሙ ነው።
መ. ሁሉም ልክ ናቸው።
(4). የትክክለኛውን መልስ ፊደል ክበብ። ቤተክርስቲያን በመመዘኛዎቹ መስማማቷ አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም

ሀ. ለቤተክርስቲያን አስተዳደርና ሕብረት መሠረት ስለሆነ።
ለ. የቤተክርስቲያኑ ተካይ የሥነ ሥርዓት እርምጃ መውሰድ የሚችልበትን ደንብ ስለሚሰጠው።
ሐ. ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመረዳትና ስሕተትን ለማስወገድ ስለሚረዳ።
መ. ክርስቲያናዊ አስተምህሮን ከዕለት ተግባራቸው ጋር እንዲያያይዙት አማኞችን ስለሚረዳ።

(5). አንድ የቤተ ክርስቲያን ተካይ ቤተ ክርስቲያኒቱ ራሷን እንድታስተዳድርና ጽኑ መሠረት እንዲኖራት ማገዝ የሚችለው

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልስ

6. ሀ. 2) የቤተክርስቲያን ተካይ
   ለ. 3) የቤተክርስቲያን አባሎች
   ሐ. 5) የቤተክርስቲያን ቦርድ
   መ. 1) የአባልነት ኮሚቴ
   ሠ. 5) የቤተክርስቲያን ቦርድ
   ረ. 4) የመማክርት ኮሚቴ

1. ሀ. 1) አዲስ አማኞች
   ለ. 1) አዲስ አማኞች
   ሐ. 2) የቤተክርስቲያን ተካይ
   መ. 1) አዲስ አማኞች
   ሠ. 2) የቤተክርስቲያን ተካይ
   ረ. 2) የቤተክርስቲያን ተካይ

7. መልስህ ከሚከተሉት ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል።
   ሀ. ሰዎች ለዘመናቸውና ስባሕላቸው የሚያስፈልግ ምሪት ከእርሱ እንዲቀበሉ መንፈስ ቅዱስ ስለፈለገ ነው።
   ለ. የአካባቢያቸውን ሰዎች ያውቃሉ፤ ውሳኔያቸው ከቤተክርስቲያን መሥራቹ ውሳኔ የበለጠ ተቀባይነት ይኖረዋል።
   ሐ. በአካባቢው በተለመደው የአመራረጥ መንገድ።
   መ. የአጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱ አማኞች።
   ሠ. ከመጋቢው ጋር አብረው ይሰራሉ ወይም ስለ ችግሩ ለመወያየት ይሰበሰባሉ፤ ለመጸለይ፤ ለመንፈሳዊ ምክክርና የጠፉትን ፈልጎ ለማግኘት የእግዚአብሔርንም መንግሥት ለማስፋፋት ዕቅድ ያወጣሉ።

2. ሀ. እውነት ለ. እውነት ሐ. ሐሰት መ. እውነት ሠ. ሐሰት ረ. እውነት

8. ሀ. 3) ይፋዊ እውቅና
   ለ. 1) የቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ ስብሰባ
   ሐ. 1) የቦርድ ስብሰባ
   መ. 4) መተዳደሪያ ደንብን ማጽደቅ

3. መ

9. ሀ. እውነት
   ለ. እውነት
   ሐ. ሐሰት
   መ. እውነት
   ሠ. እውነት
   ረ. ሐሰት
   ሰ. እውነት
   ሸ. እውነት

4. ሀ፣ ሐ እና መ

10. ከጌታ ጋርና ከወንድሞቹ ጋር የነበረው ሕብረት እንደታደሰለት ጴጥሮስ አወቀ። ምክንያቱም ኢየሱስ በእርሱ ሥራ ውስጥ ሥፍራ ስጠው።

5. ሀ

11. ሀ. እውነት ለ. ሐሰት ሐ. እውነት መ. ሐሰት ሠ. እውነት



# 4
ትምህርት

# ራስን በራስ ማስፋፋት

"ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን እንድንተክል እግዚአብሔር እየረዳን ነው። በየሳምንቱም ብዙዎች ጌታን ይቀበላሉ፤ ስለዚህ ከሕዝቡ ብዛት የተነሳ ቀድሞ በምንሰበሰብበት ሥፍራ መሰብሰብ የምንችል አይመስለኝም። ወንድም ላንካ አዲሶቹን አባሎች ለውሃ ጥምቀትና ለቤተክርስቲያን አባልነት እንድናዘጋጅ እየረዳን ነው፤ እግዚአብሔር ይመስገን" በማለት ዳዊትና ዮሐንስ ስለ ወርሃዊው እንቅስቃሴ ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወቅት ለመኩሪያ ነገሩት።

"በዚያ አካባቢ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን እየመሠረተ ነው። ለሌሎች እንዲመሰክሩና ተጨማሪ አብያተ ክርስቲያናትን እንዲያቋቁሙ አዲሶቹን አባሎች ማስተማር ያለባችሁ አሁን ነው። ካላችሁበት አካባቢ ውጪ ምንም ቤተክርስቲያን ስለሌለ ወደተለያዩ ሥፍራዎች ሄደው መመስከርና ቤተክርስቲያንን መትከል አለባቸው። ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አዳዲስ ቤተክርስቲያናትን እንዲተክሉ የጌታ ፈቃድ ነው" አለ ወንድም መኩሪያ።

እንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ማስተዳደር ቻለች ማለት ኃላፊነቷ እዚያ ላይ ያበቃል ማለት አይደለም። የክርስቶስ አካል እንደመሆንዋ ቤተ ክርስቲያን ተልዕኮዋ ሌላ ቤተ ክርስቲያን መትከል እንደሆነ ማወቅ አለባት። አዲሶቹ አማኞች ራሳቸው እንዴት አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን መትከል እንደሚችሉ በዚህ ትምህርት ትመለከታለህ።